# ማን ያውራ የነበረ 6

አንበሶች የራሳቸውን ታሪክ መፃፍ እስካልቻሉ ወይም እስካልጀመሩ ደርስ የአደን ታሪክ ሁሌም አዳኞችን ያወድሳል ተብሏልና የታገሉና ለሀገር የተሰዉ ከመድረክ እስከተገለሉ ድረስ ታሪካቸውንም አንደበታቸውንም ቀምተው ሊመፃደቁ የሚሞክሩ መኖራቸው አያስገርምም፡፡ ፖለቲካ ትርጉሙ ንግድ፤ ዝ ሽመታ ወይም ተክለሰብነትን ግንባታ፤ ዋሽቶና ቀጥፎ ለስልጣን መብቃት በሚል ከተወሰደ መጨረሻው ከቶም አያምርም፡፡ ይባስ ብለው ግለሰቦች እኛ ፖለቲካ ብለን በይፋ እስከምንሰማራ ድረስ በሀገሪቷ ፖለቲካ አልነበረም ብለው እስከ መለፈፍም የሚደርሱበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

<u>ኢሕአፓና ፖለቲካ</u> ስንል የፖለቲካ ትርጉም ከግለሰቦች የስልጣን ጥምና ስግብግብነት በራቀ መንገዱ ቅዱስ ሊባሉ የሚችሉ መርሆዎችን ባቀፈ መንገድ የሚቀርብ ነው፡፡ ፖለቲካ ከሰው ልጅ ሕይወትና ከህብረተሰብ ኑሮ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ትላንት ፖለቲካ አልነበረም ዛሬ ፖለቲካ ብቅ አለ ማለት ስለ ፖለቲካ ምንነትና ይዘት ከቶም አለመረዳትን ያመለክታል፡፡ ለስልጣን መስገብገብም ፖለቲካ ነው፡፡ ከመንግስት አልጣላም አንገቴን ደፍቼ እኖራለሁም ፖለቲካ ነው፡፡ የፖለቲካው ይዘረተና ጠባይ ሊለያይ ቢችልም ፖለቲካ በህብረተሰቡ አባል እስከሆንን ድረስ ህይወታችንን ይቃኛል፡፡ በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን ፖለቲካና የፖለቲካ ትግል ነበረ-- ብዙም ሰው ለለውጥ ሲል ህይወቱን ገብሯል፡፡ በደርግም ዘመን ተመሳሳይ ነበር፡፡ ዛሬም የተለወጠ የለም፡፡ የፖለቲካ ምርጫንናና አሰላለፋችን ማንነታችንን ገላጭ ቢሆንም ከፖለቲካ ራቅን ያሉትም ሳይቀሩ በፖለቲካው ዓለም ያሉና አቅዋምም የወሰዱ ናቸው፡፡ ሀገር ስታለቅስ፤ ሕዝብ ሲበደል አልሰማሁም፤አላየሁም፤አያገባኝም ማለት ራሱ ፖለቲካ ነው፡፡

ኢሕአፓ ፖለቲካ ሲል የህብረተሰቡ ንቁ ዜጋ ሆኖ የሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል፤የወገኔ ሰቆቃ ይሰማኛል በሚል የሚያደርገውን የዜጋ እንቅስቃሴ ለመግለፅ ነው፡፡ በሀገራችን በተለምዶ ቦተለከ ሲባል ቀጠፈ ዋሸ ማለት ነው፡፡ በእርግጥም የዋሾዎች ፖለቲካ አለ ፡፡ ዛሬ ታሪክን እየበረዙና ሀሰትን እያነገሱ በየመድረኩ የሚወራጩት የዚህ ምሳሌ ናቸው፡፡ በአራት ማዕዘኑና ከጳጉሜም ቀንና ሰዓት እየተዋሱ በቀን 25 ሰዓት የሚዋሹ ዛሬ በፖለቲካው መድረክ ሞልተዋል፡፡ ዘግናኝ ታሪካቸውን ደብቀው ፃድቅ በሉን የሚሉ ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ ፖለቲካ ማለት የግል ጥቅምን ማሚያ ዘዴና መንገድ መስሎ ስለሚታያቸው ከመጣው ባላ/ሰልጣን ጋር ሁሉ እየሰመሩና በየአጋጣሚው ማተባቸውን እየበጠሱ የሹመት ያለህ ሲሉ ይታያሉ፡፡ እነዚህም ሆኑ ሌሎች ሲመፃደቁ ግን እኛ ፖለቲከኞች አይደለንም ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ቀዶ ጥግባ ሊያደርግ የተዘጋጀ ሀኪም የለም ሀኪም አይደለሁም ማለት ይጠበቅበታል? በፖለቲካው ትግል ገብቶ፤ድርጅት አባል ሆኖ፤ለለውጥ እታገላለሁ ያለ ግለሰብ የለም ፖለቲከኛ አትበሉኝ ማለቱ ምን ማለት ነው? ፖለቲካ አፀያፊና አሳፋሪ ነገር ሆኖ ነው? ከዚህ ተያይዞ የሚደመጠው ሌላ መመፃደቅ ደግሞ የምንታገለው ለስልጣን አይደለም የሚለው ነው፡፡ የፖለቲካ ትግል ዓላማውና ትርጉሙ ለፖለቲካ ስልጣን መታገል ነው፡፡ የፖለቲካ ስልጣን ካልተያዘ የፖለቲካ ለውጥ ማምጣት ከቶም አይቻልም፡፡ ዋናው ጥያቄ ስልጣን ለሕዝብ ወይስ ለግሰብና ለጥቂቶች የሚለው ላይ ነው፡፡ ለስልጣን መታገልም ለቀና ሕዝባዊ ሉዓላዊነት እስከሆኑ ድረስ የሚደገፍና ክቡር ዓላማ ነው፡፡

ለኢሕአፓ ፖለቲካ የትርፍ ጊዜ ስራ ወይም የጡረታ ስምሪት ሳይሆን ማንነቱን ገላጭ እንቅስቃሴው ነው፡፡ ፖለቲካ የሚሆንና ሊሆን የሚችለውን ላመግኘት የሚደረግ ጥበብ የሞላው አንቅስቃሴ ነው የሚሉም አሉ፡፡ ኢሕአፓ ግን ጉም ልጨብጥ ባይልም ይቻላልን አስቀድሞ አይቻልምን አርቆ ኮከብን ከሰማይ ሊያወርድ ማለትም የተናቀውን ሕዝብ፤ተራና ድህ የተባለውን የሀገር ጌታ ለማድረግ የሚታገል ነው፡፡ ለኢሕአፓ የፖለቲካ ሰው ለመጣው ሁሉ የሚሰግድ፤ አቅዋሙን ነጋ ጠና የሚለዋውጥና የራሱን ጥቅም የሚያሳድድ ሳይሆን በዓላማው ፀንቶ፤ መርሁን ሳይሸቅጥ፤ የሕዝብና የሀገርን ጥቅም አስቀድሞና ቢዘህም መሰረተ ፀንቶ ግትር ብሎ የሚታገል ነው፡፡ በብልጠት ሽፋን፤ግትር ባለመሆን ሽፋን፤ መርህና ሀገርን ሸጦ ለስልጣን መብቃት የኢሕአፓ ዓላማና ፖለቲካ አልነበረም ፤ ዛሬም አይደለም፡፡ ኢሕአፓን የመሰቱት ምሁሮች በአፄው ዘመን ጠባያቸውን አሳምረው ከስርዓቱ ጋር ቢነጉዱ ለሹመተ የታጩ ነበሩ፡፡ እምቢኝ አሻፈረን ብለው ለሕዝብ በመቆማቸው ሕዝባዊ የፖለቲካ ሰዎች መሆናቸውን አረጋገጡ፡፡ በዘመነ ደርግም ከስርዓቱ ጋር መሞዳሞድ ቢፈልጉ ኖሮ ደርግም ልሹማችሁ ብሏቸው ነበር፡፡ ባዕዳንም በየጊዜው ፍቃዳችንን አሟሉ እንጂ ገንዘብና ስልጣም የእናንት ትሆናለች ብለዋቸው ነበር፡፡ ፖለቲካ ትግል ጉሊት ችርቻሮ መርካቶ መርህን ማነጠፍ ነው ብሎ ኢሕአፓ ባለማመኑ በዚ ጭቃ ገብቶ ታሪኩን አላበላሸም፡፡ ዛሬም ቢሆን የኢሕአፓ ዓላማና ፖለቲካ ስልጣንን ለሕዝብ ለማጎናፀፍ እንጂ የተወሰኑ መሪዎቹንና አባላቱን ለወያኔ ፓርላማ አባል አድርጎና የመለስ ዜናዊ ቡችላ ሆኖ ለመዋረድ አይደለም፡፡

ፖለቲካ ለግሪኩ ፈላሳፋ ፕላቶ የቲዎሪ ዕውቀትን ጠያቂ ጥብብ ነበር፡፡ አፄ ኃይለስላሴ እውደዋለሁ አነበዋለሁ ይሉ የነበረው ማኪያቬሊ ደግሞ ፖለቲካን በከፋፍለህ ግዛ ዘዴ ወስኖ ከፍትህና ከፖለቲካ ጥያዌቆች ና ግቦች አርቆት ነበር፡፡ለኢሕአፓ ፖለቲካ ማለት የሕዝብን ሉዓላዊነትና የሀገርን ነፃነት ለማስከበር የሚካሄድ ትግልና እንቅስቃሴ በመሆኑ እነዚህን የሚቃረንን መቀበል ብልህ ፖለቲካ ሆኖ ሊታየው ሳይችል ቆይቷል፡፡ የፖለቲካ ስልጣን የያዘው ክፍል መንግስት ነውና በዘፈቀደ መስራቱ፤ስልጣኑን ለመጠበቅ ህግን መፃረሩ የሚጠበቅ ነው ከሚሉም ጋር ኢሕአፓ አልተስማም፡፡አይስማምም፡፡ ለምን ስርዓቱን በተቃውሞ ሰልፍ ታስጨንቁታላችሁ ከሚሉ ፖለቲከኞች ጋር አይስማማም፡፡ ኢሕአፓ ፖለቲካና ፖለቲካ ስልጣንን ከሕዝብ የበላይነት፤ሕዝብ ህገ መንግስት ባለው የበላይነት ጋር አያይዞ ይቀበላል፡፡ ስልጣን በሕዝብ ፍቃድና ድጋፍ፤ በነፃ ምርጫ እስካልተደገፈ ድረስም ህገ ወጥ ነው ይላል፡፡ ተምረናል፤ምሁር ተብለናልና፤ ወይ ሰዩመ አግዚአብሔረ ወይ ስዩመ ክላሺንኮቭ ነንና ማንም አይጠይቀን፤ስልጣናችን አይደፈርም ከሚሉትም ጋር ተቃርኖ መራራ ትግል አካሂዷል፡፡ሰፊው ሕዝብ፤ጭቁኑ ሕዝብ የሚባለው ብዙሀኑ የሀገሩና የመብቱ ባለቤት እንዲሆን የሚካሄደውም ትግል ተራ ቦለቲካ ሳይሆን ሀሁራዊና ክቡር ተልዕኮው ሲልም ኢሕአፓ ያምናል፡፡

ያልተማረ ያልተመራመረ በፖለቲካ አይሰማራ ማለት ባይቻልም የፖለቲካ ትግል ዕውቅትን ፤ፅናትን መጠየቁ አልቀረም፡፡ ሕዝብን የሚጠቅም ፖለቲካ ለመጣው ጨቋኝ ሁሉ መሳንበስ ሊሆን አይችልም፡፡ እነ አቶ ክፍሌ ወዳጆና ፋሲል ናሆም ለምሳሌ የሕዝብ ፖለቲከኞች አይደሉም፡፡ መሰሎቻቸውም እንዲሁ፡፡ የወያኔ ስረዓተ ተለጣፊዎችና አጃቢዎች፤ሹመኞቸና አጋልጋዮችም ቢሆኑ ከሕዝብ አንዓር ፖለቲከኞች ሳይሆኑ ሆድ አደር ና አልፎም ከሀዲዎች ናቸው፡፡ የእነሱ ፖለቲካ ፀረ

ሕዝብ ነው፡፡ ፖለቲካ አንወድም ለሆዳችን ነው ያደርነው ቢሉም ፖለቲካቸው የከርስ ነው እንጂ ፖለቲካ መሆኑ አይሰረዝም፡፡ ኢሕአፓ ሲመሰረትና ትግም ሲጀምር ንፁህ ሕዝባዊ ዓላማና አንግቦ የጀመረውን ትግልም በማክበር ነው፡፡ በአቅዋሙ በመርሁም የፀናው የፕሮግራም ለውጥና መርህን ባለማምታታቱ ነው፡፡ ሁኔታ ሲለወጥ የፕሮግራም ለውጥን ማድረግ ተገቢና ትክክል ነው፡፡ ኢሕአፓ በየጊዜው የፕሮግራም ለውጥ ያደረገው ለዚህ ነው፡፡ ይህ ዝርዝር ነው -- ሚዛ ያለውና ኪስንም ሊቀድ የሚችል ዝርዝር ቢሆንም፡፡ መርህ ግን ሌላ ነው፡፡ ኢሕአፓ የሕዝብን ስልጣንና መበት ለማስከበርና የኢትዮጵያንም ሉዓላዊነት ለማስከበር ብሎ ያመነበትን መርህና የገባውን ቃል ኪዳን ግን አፈና ሲበዛ፣ሹመት አለሁ ሲል፣ባዕድ ሲያባብል አልቀየረም፡፡ ስለዚህም ሶስት አገዛዞችን ታግሏል፣ በመታገልም ላይ ነው፡፡ ለሶስት አገዛዝ ያደሩ ከርስ አምላኪዎች ዛሬ እየዘሙተበት ያለውም ለዚህ ነው፡፡ ፖለቲካን ከንግድ ባለማመሳሰሉ፡፡ ለግል ጥቅምና ስልጣን ሲል ለባልስልጣን ባለመጎንበሱ፡፡ ለደርግም ለወያኔም ባለመለስለሱ፡፡ ሰርቶ አደሩን ሕዝብ ባለመካዱ፡፡ የኢሕአፓ ታሪክ ሲታይ ከስህት ነፃ ሆኖ ባይገኝም ስህተቱ ሕዝብን በመክዳቱና ለገዢዎች በመጎንበሱ አይደለም፡፡ የሚታገል ኃይል፣ለሕዝብ የቆመ ኃይል በትግሉ ሂደት ሊሳሳት ይችላል፡፡ የሰማይ ቅርበቱ ለተቀማጭ ብቻ ነውና፡፡ የኢሕአፓ ታሪክ ግን ለሕዝብ መሰዋትን እንጂ ሕዝብን ክዶ ጨቋኞችን ማማከርን፣ መደገፍን የሚያንፀባረቅ አይደለም፡፡ ኢሕአፓ ፖለቲካ ማለት ኢሕአፓን በሆነው መንገድ፣ሀገርንም ወገንንም ሽጦ ለስልጣን ማበቃት ነው ብሎ አምኖ በነበረ ከማንም በፊት በስልጣን ለመሰየም ብቃቱም ችሎታውም ነበረው፡፡ ዛሬም ቢሆን ለወያኔ ተለጣፊ ሊሆን ቢያልም፣ ከመለስ ዜናዊ ተሞዳምዶ ለፍርፋሪ ቢዋደቅ ተለጣፊ ነን ከሚሉት ወራዶች ባልተናነሰ የግል ጥቅሙን ጠብቆ የመለስ ቡችላ ሆኖ በተገኘ ነበር፡፡ ይህን ዓይነት ርካሽና ወራዳ ዓላማ ግን ኢሕአፓ ከቶም የሚቀበለው አይደለምና ዛሬም ለኢሕአፓ ፖለቲካ ማለት ለሀገርና ለሕዝብ ከመታገል ጋር የተቆራኘ ሆኖ ይገኛል፡፡

ለዚህም ነው በአሁኑ ጊዜ ለሕዝብ የሚበጅና የሕዝብን መብት የሚያከብር ሁኔታ ና ለወጥ እስካልመጣ ድረስ ኢሕአፓ ለወያኔ ፀረ ዴሞክራሲ አገዛዝ ሽፋን ሰጪ ሊሆን ከቶም አይችልም፣አይፈልግም በሚል ድርጅቱ ፀንቶ የቆመው፡፡ በጊዜ ሂደት ቀስ በቀስ እንቁላልም በእግሩ ይሄዳልና ታገሱ ብለውም ከተመሰረተና ትግል ከጀመረ 33 ዓመት ያስቆጠረውን ድርጅት ሊመክሩ ለሚነሱትም ያለው ምላሽ ሀገርና ሕዝብ ከውድቀት አፋፍና ጫፍ ደርሰዋልና ትዕግስትም ቅንጦት ነው የሚል የሆነው ለዚህ ነው፡፡ በአዲስ አባባ ተንደላቀው እየ ሩና አልፎም ከወያኔ ባልስንልጣኖች ጋር አስረሽ ምቺውን የተያያዙ ተቃዋሚዎችና ምሁሮች የጎደለባቸው ስለሌለ የታገሱን ፖለቲካ ቢሰብኩ ሰፊው ሕዝብ ግን ነገ ለእሱም ለሀገሩም ምፅዓት-ውድቀት ነውና ትዕግስቱ የለውም፡፡ የኢሕአፓ ፖለቲካ ትዕግስትን የተላበሰ ቢሆንም ኢትዮጵያን ሊያጠፉ የተነሱትን ግን ትላንት እንጣላቸው ባይ ነው፡፡ ሊሞዳሞድ አለመከጀሉ ይህ ፖለቲካ ሕዝብና ሀገርን የሚጎዳ በመሆኑ ብቻ ነው፡፡ ኢሕአፓ ከሌሎች የሚለየው ፖለቲካው ለኢሕአፓ ጥቅም የተቃኘ ሳይሆን ለሕዝብና ለሀገር ጥቅም የቆመ በመሆኑ ነው፡፡ ድርጅቱ ገና ከአሁኑ አንድ ጣዖት አቁሞም በእሳቸው መሪነት ወደፊት ማለቱን ያልፈለገውም የብዙሀን ተሳታፊና ታሪክ ሰሪ ሚና እንዳይታፈን በመስጋትም ነው፡፡ ሊመለኩ ጥቂት የቀራቸው አፄ፣ ክቡር ሊቀመንበር ተብሎ ከእኔ በላይ አዋቂ ለአፈር ያለ ግብዝ ኮለኔል፣ ጓደኛቹን አፍኖና አሳዶ ብቸኛ ስልጣንን የያዘ ወያኔ ያየ ስለሆነ ፖለቲካ ስንል ከምርጦችና አቀውን ባዮች የበላይነት፣ከጥቂቶች ፈላጭ ቆራጭነት

**በፅናት ተፃረን የሰፊውን ጭቁኑን ሕዝብ የበላይነትና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር የሚካሄድ ትግልና የሚከፈልም መስዋዕትነት ማለታችን ነው፡፡ የኢሕአፓ ፖለቲካ የደርገ. የወያኔና የይስሙላ ተቃዋሚዎች ቦለቲካ አይደለም፡፡**